# መመሪያ ደንብ

የሞንጎመሪ ካውንቲ
የትምህርት ቦርድ

**ከዚህ ጋር አግባብ ያላቸው** ACD, ACF, ACH, ACH-RA, ACG, BMA, GAA, GBA-RA, GBH, GEG-RA, JHF, JHF-RA

**የሚመለከታቸው ጽ/ቤቶች፡-**
የአካዴሚ ዋና ኃላፊ
ዋና የሥራ ሀላፊ
የት/ቤት ድጋፍና መሻሻል ም/የበላይ ኃላፊ

## አለማዳላት፣ ፍትህ፣ እና ባህላዊ ብቃት

A. **ዓላማ፡-**

የሞንጎመሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች የትምህርት ቦርድ (MCPS Board of Education) ፍላጎት የሚረጋገጠው በአምስቱ ዋነኛ እሴቶች —መማር፣ ግንኙነቶች፣ መከባበር፣ —ልቀት፣ እና በእኩልነት የሚመራ የትምህርት ማህበረሰብ ለመፍጠር፤ እና ለሁሉም ተማሪዎች ለስኬታማነት የሚያበቃቸውን ድጋፍ መስጠት እና ሁሉም ሰራተኞች የላቀ ስራ የማከናወን ኃላፊነት እንዲኖራቸው ማድረግ ነው።

የቦርዱ እምነት የሚረጋገጠው እያንዳንዱ ተማሪ አስፈላጊና ተፈላጊነቱም ዋጋ ስላለው፣ በተለይም ትምህርታዊ ውጤቶች በማንኛውም ተጨባጭ ወይም ግምታዊ የግል ባህርይ ተመርኩዞ መተንበይ ስለሌለበት፣ እና ፍትኃዊነት/ሚዛናዊነት የሚረጋገጠው ለሁሉም ተማሪ ስኬታማነት ክፍተቶችን ሁሉ በማጥፋት እኩል ትኩረት በመስጠት ነው።

አዎንታዊ መመዘኛዎች/አውታር በመዘርጋትና በማስፋፋት ሁሉንም ተማሪዎች አለም-አቀፋዊ አስተሳሰብ ባለው ሕብረተሰብ ውስጥ እንዲኖሩና እንዲሰሩ ማዘጋጀት፣ እናም ግላዊ ልዩነቶችን ሁሉ የሚያቅፍ መልካም/ተስፋ ሰጭ የመማርያ አካባቢን ማጎልበት ።

የቦርዱ የማያወላውል ቁርጠኝነት እና አቋም፤ ሁሉም ሰራተኛ ባህሉ በማድረግ፤ ማንኛውንም ግለሰብ ያለበ(ባ)ትን ሁኔታ ወይም የሚገመት የግል ባህርይ የፈለገውንም ቢሆን እርስበርስ መከባበርን የተካኑ እንደሆኑ ማረጋገጥ ነው።

የቦርዱን ዋነኛ እሴቶች ለመደገፍ፣ ሁሉም የፌደራል፣ የስቴት፣ እና የአካባቢ ፀረ-አድልዎ ህጎች መከበራቸውን ማረጋገጥ።

B. **ጉዳዩ፡-**

አድልዎ በማንኛቸውም መልኩ አይፈቀድም/ችላ አይባልም። የሞንጎመሪ ካውንቲ ት/ቤቶችን (MCPS) ለእያንዳንዱ/ለሁሉም ተማሪዎች እና ሠራተኞች እናም የማህበረሰቡን ለረዥም ጊዜ የቆየ የፈጠራ ስራዎችን ማበረታት፣ ፍትሕን ማዳበር፣ አብሮነትን፣ እና ሁሉን የሚያቅፍ አሰራር እና ልማድ እንዲሰፍን መከናወን ያለባቸውን ኃላፊነቶች ይገድባል።

ሚዛናዊነት በህግ ላይ የተጻፉ ቃላትን ከመጠበቅ ባሻገር እንደሚሄድ ቦርዱ ያውቃል/ይገነዘባል። ትክክለኛ ፍትሕ፣ የወደፊቱን አስቀድሞ ማለምና ከወዲሁ ለማስተካከል ይፋ ያልተገለጹ አሉታዊ አዝማሚያዎችን፣ እና በየተቋሞቹ አብዛኛውን ጊዜ በተወሰኑ ተማሪዎች እና ሠራተኞች ላይ ያነጣጠረ/disproportionately/ መዋቅራዊ መሰናክሎችን፣ ቁልፍ የሆኑ የትምህርት ፕሮግራሞች እና የስራ መስኮች ላይ ለመሳተፍ እንዳይችሉ የሚደረግባቸውን ማእቀፎች፣ በተማሪ ዲስፕሊን ረገድም የማይገቡ እርምጃዎችን መከላከል። እርግጠኛ በሆኑ ወይም በግምታዊ የግል ባህርያት

ምክንያት ተማሪዎችና ሰራተኞች የሚደርሱባቸውን የታወቁ ኢፍትሃዊ ተፅእኖዎች ለመከላከል/ለማስቀም ሁልጊዜም በንቃት መጠበቅ ያስፈልጋል።

ለዚህ መመርያ አገልግሎት፣ ቀጥሎ ያሉት ትርጉሞች አገልግሎት ላይ ይውላሉ፡-

1. *ግላዊ ባህርይ* የሚያካትተው፤ በዘር፣ በጎሣ፣ በቀለም፣ በዝርያ፣ በትውልድ ሃረግ፣ በኃይማኖት፣ በፍልሰት አቋም/ይዞት፣ በጾታ፣ በጾታ ልዩነት፣ በጾታ መገለጫ፣ በጾታ ባሕርያት፣ በጾታ ግንኙነት፣ በቤተሰብ ይዞታ/አቋም፣ በጋብቻ፣ በእድሜ፣የአካል ወይም የአእምሮ ስንክልና፣ በድኽነት፣ በማሕበራዊና ኤኮኖሚያዊ አቋም፣ በቋንቋ፣ ወይም ሌላ በሕግ እና በሕገ መንግስት የተጠበቁ ተዛማጅነት ያላቸው ሁነቶችን መሠረት ያደረገ።

2. *የዳበረ ባህል ማለት፡-* የራስን ባህል እና የሌሎችንም ባህል በማወቅ ማሞገስ፣ መግባባት፣ እና መከባበርን ለማዳበር ቀጣይነት ያለው ሂደት ነው። በተጨማሪም በአንድ ድርጅት ውስጥ በሚገኙ ልዩ ልዩ ባህሎች፣ ተግባሮች፣ እና ግኙኝነቶች/interactions/ መገለጫዎችና አስተዋፅኦች ድርጅቱንና ማህበረሰቡን ባጠቃላይ ማጠናከርና ማበልፀግ ማለት ነው።

3. *አድሎ/ማበላለጥ፡-* በጥላቻና ቅናት ላይ የተመሰረተ በግለሰቦች ትክክለኛ ወይም ግምታዊ ባህርይ ላይ በመመርኮዝ የሚካሄዱ የጥላቻ ድርጊቶች፤ ረብሻ፣ ግዴለሽነት፣ ማንቋሸሽ፣ ማዋረድ፣ ብቀላ፣ የቃላት ስድብ፣ ንዝንዝ፣ ወከባ፣ ማስፈራራት፣ ሁከት፣ ዘለፋ፣ማራከስ/ማጥላላት፣ በጉልበት መደባደብ፣ ዝርፊያ፣ ወይም የትምህርት አካባቢ እና የስራ ሂደትን በሚያደናቅፍ ሁኔታ ንብረት ማበላሸት/ማውደም አድልዎ በተጨማሪ የሚያካትተው ላይላዩን አድሎአዊነት የሌለው የሚመስሉ ነገር ግን በግለሰብ ሃቀኛ ወይም ግምታዊ ግላዊ ባህርይ ላይ በመመስረት ምክንያታዊ ያልሆነ/የማይመስል ተፅእኖ ያላቸው ስነምግባሮች ወይም ድርጊቶችን ነው። አድልዎ ዘረኝነትን፣ ፆታዊ ትእቢተኛነት/sexism፣ እና ድርጅታዊ ስር የሰደዱ አግባብነት የሌላቸው ጥላቻዎችን ከመገለጫዎቻቸው ጋር ያካትታል።

4. *እኩልነት/ሚዛናዊነት፡-* እያንዳንዱ ተማሪ እና ሠራተኛ ባለበት ሁኔታ ወይም በግምታዊ ሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ ግላዊ ተግዳሮቶችም ቢኖሩ፣ በትጋት መሠረታዊ ነገሮችን በመወጣት ለአካደሚክ እና ለሥራ ዝግጁነት ብቁ እንዲሆኑ በመደገፍ/በማገዝ ለማበረታታት በተግባር የሚገለጽ ቁርጠኝነት ነው።

5. *ውስጠ ታዋቂ አድልዎ/Implicit bias/* የሚያመለክተው፡-በግንዛቤአችን፣ በተግባራችን፣ እና በውሳኔዎቻችን ላይ ተፅእኖ የሚያደርጉ ወግአጥባቂነት፣ የተዛቡ አመለካከቶችና፣ አቋሞችን ያመለክታል። እነዚህ አድልኦዎች፣ ተቀባይነት ያላቸውና ተቀባይነት የሌላቸውን አሉታዊ ግምገማዎችን የሚያካትት በመሆኑ፣ ሳይታሰብበት/involuntarily/ እና ግለሰቡ/ቧ ሳያውቅ/ሳታውቅ ወይም ሆን ተብሎ ሳይቆጣጠረው/ሳትቆጣጠረው ሊያደርገው/ልታደርገዉ ይችላል/ ትችላለች።

C. **አቋም**

1. ሠራተኞች በድርጊት ጥሩ የተፎካካሪነት ባህል እንዲዳብርና ለከፍተኛ ብቃት የሚያስችል፣ ትጋት እንደሚጠበቅባቸውና የሚያግዳቸውን አድሎአዊነትን/ሚዛናዊነት የጎደላቸው እንቅፋቶችን በማስወገድ ሁሉንም ተማሪዎች ለከፍተኛ ስኬታማነት እንዲበቁ በማዘጋጀት ያለውን ክፍተት የማጥበብ ትጋት ዲስትሪክቱ እንደሚያዳብርና እንደሚያራምድ ቦርዱ ይጠብቃል ።

2. ቦርዱ የሚጠብቀው፤ ሁሉም ተማሪዎችና ሰራተኞች የግለሰብ ሃቀኛ ወይም ግምታዊ የግል ባህርያትን ሳይመለከቱ እርስበርስ በመከባበር ራሳቸውን በስነስርአት እንዲገዙ ነው።

3. ቦርዱ በሃቀኛ ወይም ግምታዊ የግል ባህርይ ምክንያት በግለሰቦች፣ በተማሪዎችና በሰራተኞች የሚፈፀም፣ ማንኛውንም አይነት አድልዎ ይከለክላል/አይፈቀድም።

4. ቦርዱ ይህ መመሪያ እንደ ሞዴል እንዲያገለግል ወስኗል። በዚህ ፖሊሲ ላይ የሚጠበቀው፤ ሁሉም የቦርድና የMCPS ዘገባዎች፣ አቀራረብ፣ እና ውሳኔ አሰጣጥ የዚህን መመርያ ሚዛናዊነት /implications/ ውጤት ታሳቢ እንደሚያደርጉ ነው።

5. እንዲሁም ቦርዱ የሚከተሉትን ይጠብቃል እናም ያራምዳል፡-

a) በሰራተኞች፣ በተማሪዎች፣ በወላጆች/አሳዳጊዎች፣ እና በህብረተሰቡ መካከል የሚደረግ ትብብር፡-

(1) ሰራተኞች ከተማሪዎች ጋር፣ ከወላጆች/አሳዳጊዎች ጋር፣ እና ከማህበረሰብ አባላት ጋር አብረው በመስራት እያንዳንዱ ት/ቤትና የስራ ቦታ ከአድልዎ የነፃ መሆኑን ማረጋገጥ ይጠበቅባቸዋል።

(2) ወላጆች/አሳዳጊዎች በህግ የተቀመጡና በዚህ ፖሊሲ-መመሪያ ላይ የተንፀባረቁ እምነቶች፣ ሃሳቦች፣ እና ግዴታዎች የሚተገበሩ እና የፀኑ እንደሆነ ልጆቻቸውን እንዲያበረታቱ እና ፅኑ እምነት እንዲመሰርቱ እናደፋፍራለን፣ ከዚህ በላይ የተገለጹ/የሚጠበቁትን ለማሟላት ከMCPS ሰራተኞች ጋር እንዲተባበሩ እናበረታታቸዋለን።

(3) ሰራተኞች ሃቀኛም ይሁን ወይም ግምታዊ ግላዊ ባህሪያትን ሰበብ ሳያደርጉ ሁሉንም ወላጆች/አሳዳጊዎች በልጆቻቸው ትምህርት እና ስራ ተሳትፎ እንዲኖራቸውና ተግባራዊ ተሳትፎአቸውን የሚያደናቅፉ ገደቦችን ለማስወገድ እንዲሰሩ ይጠበቅባቸዋል።

(4) MCPS በሥራ ግብረኃይል፣ በኮሚቴዎች፣ ሀላፊነት ተሰጥቷቸው የሚሰሩ (ኮሚሽን)፣ እና የልዩ ልዩ ማህበረሰቦችን፣ ባህል፣ ቋንቋዎች፣ እና አመለካከቶችን የሚወክሉ የሌሎችንም አማካሪ አባላትን ጉልህ ተሳትፎ ይፈልጋል።

b) በትምህርት እድሎች እኩል ተጠቃሚ መሆን።

(1) ቦርዱ ለተማሪዎች ስኬት ወሳኝ የሆኑ የልዩነት ደረጃዎችንና የተዛቡ አሰራሮችን ለማስተካከል ቁርጠኝነት አለው፣ በተጨማሪ፡-

(a) መገልገያዎች፣ ጠንካራ/ጠጣር የፈጠራ ኮርሶች፣ ፕሮግራሞች፣ እና ከቀለም ትምህርት በተጨማሪ የሚካሄዱ እንቅስቃሴዎችን ጨምሮ፤

(b) ውጤታማና ብቃት ያላቸው መምህራን፣ መሪዎች፣ እና የድጋፍ ሰራተኞች፤

(c) አጥጋቢ መገልገያዎችና መሳሪያዎች፤

(d) ወቅታዊ ቴክኖሎጂ፤

(e) ጥራት ያላቸው የትምህርት ቁሳቁሶች፤ እና

(f) ተመጣጣኝ/በቂ ገንዘብ/የገንዘብ ድጋፍ።

ይህ ቃል መግባት ቀጣይነት የሚኖረውና፣ የበለጠ ለሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች ተጨማሪ ገንዘብ ለማቅረብ የታሰበበት ስልት /intentional strategy of providing additional funding to students in greater need/፣ እንዲሁም በይበልጥ ችግር ያላቸው በርካታ ተማሪዎችን ለሚያገለግሉ ት/ቤቶች /schools that serve larger numbers of students in need/መገልገያዎች (resources) እንዴት እንደሚመደቡ የሚያረጋገጥ ነው።

(2) በMCPS መዋቅራዊና በተቋማት በሁሉም ት/ቤቶች ውስጥ ያሉ ተማሪዎች በእኩልነት/በሚዛናዊነት ማግኘት የሚገባቸውን የትምህርት እድሎችን የሚከለክሉ እንቅፋቶችን/መሰናክሎችን ለይቶ ለማወቅና ችግሮቹን ለማስወገድ ይሰራል።

(3) MCPS የዲሲፕሊን ውጤቶች የፍትሃዊ አስተዳደር ይዘት አንድ አካል/ግብአት በመሆኑ በት/ቤቶች ትክክለኛ የትምህርት እድሎችን ለማግኘት ተገቢ እንደሚሆን ይጠበቃል።

(4) MCPS የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች ቋንቋ ባለመረዳት ምክንያት የሚያጋጥሟቸውን መሰናክሎች እና ሌሎችንም እንቅፋቶች በማስወገድ በት/ቤቶቻቸው የትምህርት ፕሮግራሞች ላይ ትርጉም ያለው ተሳትፎ ለማድረግ እንዲችሉ ለማድረግ ቀዳሚ እርምጃዎችን ይወስዳል። MCPS፣ እርግጠኛ ወይም ግምታዊ የሆኑ የግል ባህርያትን ምክንያት ሳይደረግ፣ በት/ቤቶች መካከልና በተመሳሳይ ት/ቤት ውስጥ በሚገኙ ተማሪዎች መካከል በሁለቱም ከበድ/ጠንከር ያለ የኮርስ ስራ እና ተመጣጣኝ ኣካዴሚያዊ ፕሮግራሞች እኩል ያቀርባል።

(5) MCPS፣ በታሪክ ተያይዘው የመጡ ወግአጥባቂ አስተሳሰቦች ሳይገድቡት፣ ሁሉም ተማሪዎች ግቦቻቸውንና ፍላጎቶቻቸውን እንዲያከናውኑ ያበረታታል። ተማሪዎች በርካታ ከፍተኛ ተፎካካሪነት በሚገጥማቸው ፕሮግራሞች ላይ ለመግባት እና፣ ልዩ ልዩ የት/ቤት እንቅስቃሴዎች፣ አትሌቲክስን ጨምሮ፣ ከስርኣተ ትምህርት-ውጭ አካዴሚያዊ ባልሆኑ ፕሮግራሞች፣ አመለካከታቸውን ለማበልጸግ እና ትርጉም-ያለው አርኪ ስራ በመረጡት መስክ ለመሳተፍ የተለያዩ በርካታ እድሎች ይሰጣቸዋል።

(6) MCPS ት/ቤቶችን፣ የመማሪያ ክፍሎችን፣ የሥራ ቦታዎችን፣ እና በት/ቤቶች ስፖንሰርድ ሆነው የሚያካሄዱ (mascots, logos, team names, chants, or musical accompaniments) ጨምሮ ሁሉን የሚያካትቱ እና ከአድልዎ-የፀዳ፣ እና ለሁሉም ምቹ ሁኔታን ያበረታታል/ያስፋፋል።

(7) MCPS ብዝሃ ማህበረሰባችንን የሚወክል ከቅድመ-ሙአለ ህፃናት እስከ 12ኛ ክፍል (Pre-Kindergarten to Grade 12) በማህበረሰባችን መካከል ሚዛናዊነትን የጠበቀ፣ ፍትህ፣ መከባበር፣ እና ትሕትና፣ የሰፈነበት ስርዓተ ትምህርት ስለ ዓለምአቀፋዊ ማህበረሰብ በጎ አስተዋጽኦ የሚገልጽና ሚዛናዊነትን የሚወክል፣ ለሠራተኞች እና ለተማሪዎች በእያንዳንዱ ት/ቤት እና ፕሮግራም ምሳሌያዊ የሆነ የትምህርት ባህል የሚዳብርበት እድል ይሰጣል። ስርአተ ትምህርቱ ሰራተኞች አርአያ/ሞዴል እንዲያደርጉ እና ተማሪዎች የሚከተሉትን አመለካከቶች፣ ክሂሎቶች፣ እና ስነምግባሮች እንዲያዳብሩ ያስችላል፦

(a) የራስን ቅርስ ዋጋ በመስጠት የሌሎችንም ቅርስ ማክበርና ዋጋ መስጠት

(b) መከባበር፣ ልዩነቶችን ዋጋ በመስጠት ማክበር፣ ጤናማ እና በማህበረሰብ ውስጥ ሊያብብና ሊዳብር የሚገባ አስፈላጊ ግብአት ነው።

(c) ለባህላዊ ብዙሃነት ብልጽግናና ለአብሮነት ዋጋ መስጠት፤

(d) የአብሮነት ግንኙነቶችን ማዳበርና ሕብረ- ባህላዊ አካባቢዎች ላይ በውጤታማነት መስራት፤ እና

(e) ሰዎች በግለሰቦች ሁኔታ ወይም ግምታዊ ባህርይ ምክንያት በሌሎች ላይ ያላቸውን ወግአጥባቂ/ጅምላ አመለካከትን መቋቋም እና ማስወገድ።

(8) የMCPS ት/ቤቶች አገልግሎት ላይ የሚውሉ የትምህርት ቁሳቁሶች አለም-አቀፋዊ ሀብረተሰብን፣ብዝሃነትን፣ የሴቶች ትልቅ ጉጉት፣ ያልተፈቱ ጉዳዮች፣ እና ስኬታማነታቸውን /the aspirations, issues, and achievements of women /፣ ስንክልና ስላላቸው ግለሰቦች፣ እና ስለ ተለያየ ዘር፣ ትውልድ፣ እና ባህላዊ አመጣጣቸውን ያንጸባርቃሉ።

c) በመዋቅራዊ ስርአት ውስጥ የተዘረጋ ባህልን ለማሳካት ስልጠናና ትምህርት።

MCPS፣ ባህላዊ ብቃትን ለማዳበር በሰራተኞች፣ በወላጆች/አሳዳጊዎች፣ እና በማህበረሰብ አባሎች መካከል ውጤታማ የመተባበር እድሎችን በመፍጠር፣ መዋቅራዊ ተሳትፎና ትብብሮችን በማጎልበት ልዩነቶችንና አለመግባባቶችን እንዲፈቱ ያበረታታል።

(d) በእኩልነት ስራ የመቀጠር እድሎች።

(1) MCPS ብዙሃነትን ያቀፈ የሰራተኛ ሃይል ተሳትፎ እንዲዳብር መከታተልና በሁሉም የሰራተኛ አቀጣጠር ስራዎች ሆን ተብሎ ከሚደረግ ጥላቻና አድልዎ ነፃ የሆነ ዲስትሪክት ለመፍጠር ተገቢ እርምጃ መውሰድ ይቀጥላል።

(2) MCPS ብዙሃነትን ያቀፈ የሰራተኛ ሃይል በመመልመል፣ በመቅጠር፣ በመያዝ/ማቆየት፣ እና በማሳደግ ረገድ የተደቀኑ መዋቅራዊ ገደቦችን ለማስወገድ አዎንታዊ እርምጃዎችን ይወስዳል።

(3) MCPS የብዙሃነት ተሳትፎ/ውክልና በጣም ቀንሶ የሚታዩባቸውን የስራ ቦታዎች በመለየት እናም፣ የድርድር ስምምነቶች የተጠበቁ ሆነው፣ ብቃት ያላቸውን እጩዎች በመመልመል እና/ወይም በማሳደግ ብዙሃነት/diverse/ የሰራተኛ ሃይል እንዲጎለብት ያደርጋል። ለምሳሌ:- MCPS በፆታ ምክንያት በተለምዶ የማይፈቀድላቸው ቦታዎች ላይ መመልመል/ስራ ማስያዝ ይቀጥላል።

(4) ከእኩዮቻቸው፣ ከተማሪዎች፣ ከወላጆች/አሳዳጊዎችና የማህበረሰብ ኣባላት ጋር በሚከናወኑ እለታዊ ግንኙነቶች በዚህ መመርያ የተገለፁ የቦርዱን ዋነኛ እሴቶችና እምነቶችን እንዲያራምዱ MCPS ሰራተኞችን ኃላፊነት ይሰጣቸዋል።

D. **ተፈላጊ ውጤቶች**

1. እያንዳንዱ ት/ቤት እና የሥራ ጣቢያ በቦርዱ መሠረታዊ እሴቶች/እምነት ላይ የተመሰረተ መግባባት፣ መከባበር፣ ትሕትና፣ መቀባበል፣ እና በሁሉም ግለሰብ እና ቡድኖች ዘንድ መልካም ግንኙነትና የመከባበር ባህልን መተግበር ይጠበቅበታል።

2. የትምህርት እና በእኩልነት ስራ የመቀጠር እድሎችን የሚገድቡ መዋቅራዊና ድርጅታዊ ተፅእኖዎች ይወገዳሉ።

3. የMCPS ት/ቤቶችና የስራ ቦታዎች ከጥላቻ፣ ከአመፅ/ረብሻ፣ ከግድየለሽነት፣ እና ከንቀትና የአድልዎ ትግባሬዎች ነፃ ይሆናሉ።

4. የትምህርት ውጤቶች በትክክል ወይም በግምታዊ ግላዊ ባህሪዎች የሚተነበዩ አይሆኑም፣ በተማሪ ስኬታማነት ላይ የሚታዩ ክፍተቶችም በሚያመረቃ ሁኔታ ይቀነሳሉ።

5. የMCPS ተማሪዎች እና ሠራተኞች በሕብረተሰቡ መካከል ትሕትናን፣ መቀባበልን፣ መከባበርን፣ እና መልካም ግንኙነትን በማስተጋባት ጥሩ ተምሳሌትነት ይኖራቸዋል።

6. የሁሉም ተማሪዎች የትምህርት ተሞክሮዎች የማህበረሰቡን ብዙሃዊነት ባህርይ በማንፀባረቅ ይበለፅጋሉ ብዙሃዊነትን ከሚያንፀባርቁ ወገኖች በመጡ ሰራተኞች አማካኝነት፤ የብዙሃነትን ግንዛቤ ለሚያራምድ ትምህርት ሁኔታዎችን ማመቻቸት እና በትምህርት ሁኔታ/አቀማመጥ ውስጥ ለሚገኙ ለተፈጥሮአዊ ሃሳቦች ልውውጥ ጥራት አስተዋፅኦ ማድረግ።

E. **የአፈፃፀም/የትግበራ ስልቶች**

1. ከፍተኛ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች፣ እንዲሁም በይበልጥ ችግር ያላቸው በርካታ ተማሪዎችን ለሚያገለግሉ ት/ቤቶች፣ ተጨማሪ ገንዘብ ለመስጠት የታለመ ስልትን መተግበር እና ለተማሪዎች ስኬት ወሳኝ የሆኑ መገልገያዎችን በማሟላት የተዛቡ አመለካከቶችን ቦርዱ መፍትሔ ይሰጣል።

2. MCPS የዚህ መመርያ ሀሳቦችን በምሳሌነት ባህል ለመገንባትና ለማስፋፋት ከሰራተኞች፣ ከተማሪዎች፣ ከወላጆች/አሳዳጊዎች፣ እና ከማህበረሰቡ በሞላ ጋር አብሮ ይሰራል።

3. MCPS በርካታና አስፈላጊ የሆኑ ጠቋሚ ሁኔታዎችን የተማሪዎችን ውጤቶች፣ ተሳትፎዎች/ስራዎች፣ እና የት/ቤትን አጠቃላይ ሁኔታ፣ እና ለተማሪ፣ ለት/ቤት፣ እና ለዲስትሪክት-አቀፍ አፈፃፀም ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ አስፈላጊ የሚሆኑ ልዩ አሃዞችን በመቆጣጠር፤ በውጤቶች መሃከል የሚታዩ ልዩነቶችን ለመቀነስ፤ እና አካዴሚያዊ ውጤቶች በግምታዊ ወይም ግላዊ ባህርይ የሚተነበዩ እዳይሆኑና ተገምግመው በግልፅ ለህዝብ ተለይተው ሪፖርት የሚቀርብ መሆኑን ማረጋገጥ ።

4. ፕሮግራሞች፣ ስርአተትምህርት፣ የትምህርት ቁሳቁሶች፣ እና እንቅስቃሴዎች፣ አትሌቲክስ፣ ከትምህርት ጊዜ ውጭና አካደሚያዊ ያልሆኑ ፕሮግራሞችና እንቅስቃሴዎችን ጨምሮ፣ ለሁሉም ተማሪዎች በየጊዜው እየጨመረ የሚሄደውን ብዙሃነት በካውንቲ፣ በስቴት፣ በአገር፣ እና አለም ውስጥ አብሮ ለመኖርና ለመስራት እውቅት፣ ክሂሎቶች፣ እቋሞች እና ስነምግባሮችን ያጎናጽፏቸዋል።

5. MCPS ለሙያዊ እድገት በሚሰጥ ስልጠና፤ ሁሉም ሰራተኞች ባህላዊ ብቃት ክሂሎቶች፣ እውቀት፣ እና እምነት እንደሚኖራቸው ለማረጋገጥና ተማሪዎችን ያማከለ ማህበራዊ፣-ስሜታዊ፣ እና የተማሪዎችን አእምሮአዊ ጤንነት፣ እና ግላዊና የተለያዩ ፍላጎቶችን የሚያሟሉ የመማርያ አካባቢዎችን ለመፍጠር የሚያስችል ትምህርት ያቀርብላቸዋል።

6. በሁሉም ሰራተኞች፣ ተማሪዎች፣ ወላጆች/ኣሳዳጊዎች፣ እና የማህበረሰብ ኣባላት መካከል ሁልጊዜ አክብሮትና ትህትና የተሞላበት ውይይትና ግንኙነቶችን ለማበረታታት ሰራተኞች እንግዳ ተቀባይ ኣካባቢዎችን ለማሳደግ፤ እናም ቤተሰቦች በልጆቻቸው ትምህርት ጉዳይ ከመሳተፍ የሚከለክሉ ባህላዊ ወይም የቋንቋ መሰናክሎችን ለማስወገድ አስተርጓሚዎችና፣ የተተረጎሙ ሰነዶችን የመሳሰሉ፣ መገልገያዎችን ይጠቀማሉ።

7. አድልዎን ለመከላከል ስልቶችን በመጠቀም እናም፣ የአድሎአዊነት ችግሮች ከተከሰቱ የመፍታት፣ የመከታተል፣ እና የመተንተን ሂደቶች ተግባራዊ ይደረጋሉ።

8. MCPS፣ ከሞንጎመሪ ካውንቲ አስተዳደር/አስፈጻሚ አካል፣ ከሞንጎመሪ ካውንቲ ካውንስል፣ ከየአካባቢ የህግ አስፈጻሚ ኤጀንሲዎች፣ ሌሎች የካውንቲው ኤጀንሲዎች፣ የማህበረሰብ ቡድኖች፣ የንግድ ድርጅቶች፣ እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር ለተማሪዎች እና ለሰራተኞች ሚዛናዊነትን/እኩልነትን ለማዳበር እና አድሎአዊነትን ለመቀነስ በመተባበር ይሰራል።

9. ይህን የቦርዱን ፀረ-አድልዎ መመርያ-ደንብ የሚያጠቃልል መርህ በMCPS ህትመቶች እና በMCPS ድረ-ገጾች በተቀዳሚነት ይካተታሉ። የቦርዱን ፀረ-አድልዎ መመርያ-ደንብ በእንግሊዘኛ የተዘጋጀ ህትመት በMCPS ተማሪዎች፣ ወላጆች/አሳዳጊዎች አዘውትረው በሚጠይቋቸው ቋንቋዎች ትርጉሞችና የትርጉም አገልግሎቶች ተዘጋጅተው ይቀርባሉ።

10. የት/ቤቶች የበላይ ተቆጣጣሪ ይህንን-ደንብ ለመተግበር አግባብ ያለው መሪ ጽ/ቤት ይሰይማል፡- እና ከሌሎች ጽ/ቤቶችም በአግባቡ ድጋፍ እየተሰጠ የሚከተለውን ኃላፊነት በመውሰድ፣

    a) የፌደራል፣ የስቴት፣ እና የአካባቢ ፀረ-አድልዎ ህጎች በሙሉ በMCPS መከበራቸውን መቆጣጣርና ማረጋገጥ፣

    b) የአድልዎ ቅሬታዎችን ወድያውኑ ማጣራትና መፍታት፣

c) በዚህ መመሪያ ስር የቦርዱን እሴቶችና የሚጠበቁ ሥርዓቶችን ግንዛቤ ከፍ ማድረግ፣

d) የፍትሃዊነትና ሚዛናዊነት ባህልን እንዲዳብር ስልጠናዎችን መስጠትና በያሉበት በመድረስ፣

e) ፋይዳ ያላቸው/ተገቢ ዘገባዎች እንዲጠበቁ ማድረግ።

11. የት/ቤቶች የበላይ ተቆጣጣሪ በዚህ መመርያ የተገለፁትን እሴቶችና መመሪያዎችን በመጣስ የተመሰከረበት/የተመሰከረባት፣ የደንታቢስነት ስነምግባር የሚያሳይ/የምታሳይ ሰራተኛን ባህላዊ ብቃትን በሚመለከት ተጨማሪ ስልጠና እንዲሳተፍ ለማድረግ ይችላል። ቀጣይ ደንታቢስነት በትምህርት ቦርድ ተቀባይነት አይኖረውም ስለሆነም በሰራተኛ የስነምግባር ኮድ መሰረት፣ ስንብትን ጨምሮ ተጨማሪ የዲሲፕሊን እርምጃ ሊያስከትል ይችላል።

F. **ግምገማ-ክትትል እና ሪፖርት**

1. የት/ቤቶች የበላይ ተቆጣጣሪ የዚህን-ደንብ ተግባራዊነት እና የቦርዱን ዋነኛ እሴቶች የሚያሟላ ፍትሃዊ የት/ቤት ስርአት ለመፍጠር ዲስትሪክቱ የሚያካሂዳቸው ጥረቶችን በሚመለከት ወቅታዊ ዘገባዎች ለህዝብና ለቦርዱ ያቀርባል።

2. ይህ ደንብ በትምህርት ቦርድ የአፈፃፀም ሂደት መሠረት ስለተግባራዊነቱ ግምገማ ይደረግበታል።

**ከዚህ በታች የተዘረዘሩ ተዛማጅ ምንጮችን ይመልከቱ፡-** በመከባበር ላይ የተመሰረተ ባህል "Culture of Respect Compact"[1]; የሞንጎመሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች *የተማሪ ስነምግባር ኮድ "MCPS Student Code of Conduct"*, የሞንጎመሪ ካውንቲ ት/ቤቶች *የሠራተኛ ስነምግባር ኮድ "MCPS Employee Code of Conduct"*; የሞንጎመሪ ካውንቲ ት/ቤቶች *የሃይማኖት ብዝሃነትን ስለማክበር መመሪያ "Guidelines for Respecting Religious Diversity"*; በዚህ ፖሊሲ በመጨረሻው ግርጌ የተዘረዘሩትን ከፌደራል እና ከስቴት ጋር የተገናኙ ምንጮችን ይመልከቱ፡- የዩ.ኤስ ህገመንግስት ማሻሻያ 14፣ ርእስ VI ስለ ሰብአዊ መብቶች ድንጋጌ 1964,42U.S.C፣ 2000d et seq፣ U.S. Constitution, Amendment 14; Title VI of the Civil Rights Act of 1964, 42 ርእስ VII የሰብአዊ መብቶች ድንጋጌ 1964፣ 42 U.S.C., 2000e et seqU.S.C., 2000d et seq; የተሻሻለውን, 42 U.S.C., 2000e et seq; ርእስ IX የትምህርት ማሻሻያ ድንጋጌ 1972, 20 U.S.C. 1681 et seq; 34 የፌደራል ህጎችን ኮድ Code of Federal Regulations (CFR), ክፍል 106, 34 CFR ክፍል 100; ስለ አካለስንኩላን ትምህርት ድንጋጌ(IDEA), 20 U.S.C. 1400-1487; ክፍል 504 ስለተሐድሶ/መልሶ ማቋቋም ድንጋጌ 1973, የተሻሻለውን, 29 U.S.C. ክፍል 794; በአካለ ስንክልና ስለሚኖሩ አሜሪካውያን ድንጋጌ(ADA), 42 U.S.C. 12131 et seq; ክፍል 1981 ስለዜጎች መብት ድንጋጌ 1866, 42 U.S.C. § 1981; በእድሜ ምክንያት ስራ ላይ አድሎአዊነትን የሚከለክል ድንጋጌ 1967, 29 U.S.C. §§ 621-634; ስለ እኩል ክፍያ ድንጋጌ 1963, 29 U.S.C. § 206(d); በሜሪላንድ ህገመንግስት ስለ መብቶች ማሻሻያ ድንጋጌ ላይ ስለ እኩልነት/እኩል መብት (አንቀጽ 46)Equal Rights Amendment to the Maryland Constitution's Declaration of Rights (Article 46); የሜሪላንድ ህግ ማብራሪያ ኮድ፣ የስቴት መስተዳድር ድንጋጌ አንቀጽ/ርዕስ 20፣ Annotated Code of Maryland, State Government Article, Title 20; ስለ ህሙማን ጥበቃ ተመጣጣኝ እንክብካቤ ደንብ/Patient Protection Affordable Care Act, 42 U.S.C. § 18001 et seq; የሚሪላንድ ማብራሪያ ኮድ የትምህርት ደንብ አንቀጽ 6-104, 7-424.1፣ "Annotated Code of Maryland, Education Article 6-104, 7-424.1; የሜሪላንድ ህጎች/ደንቦች ኮድ "COMAR 13A.05.01"

---

[1] *Culture of Respect Compact/በመከባበር ላይ የተመሰረተ ባህል በMCPS፣ የሞንጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ማህበር፣ አለም-አቀፍ የአገልግሎት ሰራተኞች ማህበር Local 500፣ እና የሞንጎመሪ ካውንቲ የአስተዳዳሪዎችና የርእሰመምህራን ማህበር መካከል*

*የፖሊሲው አመጣጥ፡-* Adopted by Resolution No 595-69, November 11, 1969; amended by Resolution No 16-72, January 11, 1972; amended by Resolution No 536-77, August 2, 1977; amended by Resolution No 240-96, March 25, 1996; amended by Resolution No 323-96, May 14, 1996; amended by Resolution No 249-03, May 13, 2003; amended by Resolution No 318-17, June 26, 2017.